# ሐቀኛ ሰው ይፈለጋል

ሰው ሲባል በሥራ ሒደት በኩል ሁለት ገጽ ያለው ሁኖ ይታያል አንደኛው ይፈለጋል የተባለው ሰው የራሱን ጥቅም በመናቅ የአገሩንና የወገኑን እድገቱንም ሆነ ጥቅሙን የሚወድ ሀብቱን ብቻ ሳይሆን ሕይወቱንም ጭምር ቤዛ አድርጐ አሳልፎ የሚሰጥ በመሆኑ በየጊዜው ለሚነሳው ትውልድ የሚያስመሰግን የሥራ ቅርስ ትቶ ስለሚያልፍ ሥራው ብቻ ሳይሆን ስሙም ከመቃብር በላይ ይውላል ።

ስለእንዲህ ያለው ሰው አንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ሲናገር «ሠርቶ የሚያሠራ ሰው ራሱን በመጥላት፤ ሌላውን በመውደድ ፤ ገንዘቡንም ፤ ሕይወቱንም ሊሀገሩ መስዋዕት አድርጐ በማቅረብ የምግባርና የእምነት መልእክተኛ ሆኖ ሁሉን ለማገልገልና ለመርዳት ሠርቶ ለማሠራት ወደ ሥራ ዓለም እራሱ ይሰማራል ሌላውንም ያሰማራል ፤ ካለ በኋላ አስተያየቱን በመቀጠል እንዲህ ያለው ሰው በዚህ ብቻ ሳይወሰን በሕዝቡ መካከል እየተገኘ የተጣሉትን በማስታረቅ ያልተማሩትን በማስተማር የሰላም ሐዋርያ ሆኖ ኅብረተሰቡን አቅሙ በፈቀደለት መጠን ያገለግላል ሰው ይሏችኋል ይህ ነው» ብሎአል ።

እርግጥም ሥራ ራሱ ምስክር ሁኖ ስለሚመሰክር የሰው ምስክር አያሻውም ሲባል ከእውነት ፈቀቅ አይልም። ለምሳሌ ሽቱ በአገልግሎቱ የታወቀ ነው ከዚህም የተነሳ መዓዛው ከአራቱ ማዕዘን በኩል በነፋስ ኃይል እየሄደ ይውዳል በጠረኑ የሰውን ልብ ሲያስደስት ሲያስጐመጅ አድናቆትንም ሲያበረክት ከመታየቱም በቀር በሰው ዘንድ ኃይሉ ሳይበርድ ስሜቱ ሳይቀዘቅዝ ተወዳጅነት ይዞ መኖሩ ለማንም ግልጽ ነው ።

ሠርቶ የሚያሠራ ሰውም ለሠራተኞችም ሆነ ለመልካም ሥራ የጥሩ ሽቱ ተመሳሳይ ስለሆነ በሥራ መዓዛ ሰዎችን ወደ ሥራ ዓለም ይስባል ሥራውም በአራቱ መዓዘን እያወደ ሠራተኞች ሁሉ ሥራን እንዲወዱ ያደርጋል።

ሁለተኛው ደግሞ የማይፈለግ ሰነፍ ሰው ራሱን በመውደድ ለማኅበራዊ ኑሮ ሳይሆን ለግል ጥቅሙ ብቻ እየተስገበገበ አገሩን ወገኑን የሚጠቅምበትን ራሱ በሰው ዘንድ የሚመሰገንበትን አንዳች ሥራ ሳይሠራ ይኖራል። እንዲህ ያለውም ሰው እንደ እቡት ትል ጥቅምን ሁሉ ለራሱ ሰብስቦ ወንድሙ የሱ ለማኝ የሱ አሽከር በመሆን እጁን እየዘረጋ እሱን ሲለምን እንዲኖር የሚፈልግ በመሆኑ ለኅብረተሰቡ ታላቅ በሽታ ነው ። እንዲህ ያለውንም ሰው ኅብረተሰቡ አይፈልገውም ።

ዲዮጋን የተባለው የግሪክ ፈላስፋ እኩለ ቀን ሲሆን ፀሐይ ብርሃንዋን በኃይል በምትሰጥበት ጊዜ የሰው ብዛት በሚገኝበት በአቴና ከተማና በየገቢያው ሙብራት እያበራ ይዞ ጀመር የተመለከቱትም ሰዎች ሁኔታው ስላስገረማቸው «በቀን ለምን ታበራለህ?ብለው ቢጠይቁት ሰው እየፈለኩ ነው አላቸው ። ይህ የምታየው ሁሉ ሰው አይደለምን ? አሉት እሱም ይህ ሁሉ ለሀገር ለወገን የማይጠቅም እውነትንም ፤ ሰላምንም የሚፈልግ አይደለም ስለራሱ ጥቅም ብቻ የሚስገበገብ ሒቀኝነትን ፤ ጨዋነትን ትቶ ሌላውን የሚበዘብዝ ፤ ባጭበርባሪነት፤ በአታላይነት የሚኖርና በሐሰት እየማለ የሰውን ገንዘብ የሚነጥቅ ፤ ፍርድ አጉዳይ ፤ በውሸት መስካሪ ፤ ስለሆነ እንዲህ ያለው ሰው አይፈለግም እኔም ሆንኩ አገሪትዋ በመብራት የምንፈልገው እውነተኛ ሰው ነው» ብሏል።

መዝሙረኛው ዳዊትም ይህን አስተያየት በመደገፍ ፤ አቤቱ በድንኳንህ ማን ያድራል ? በማለት ፈጣሪውን በጸሎት ከጠየቀ በኋላ እራሱ ጥያቄውን ሲመልስ በቅንነት የሚሄድ ጽድቅንም የሚያደርግ ፤ በልቡም እውነትን የሚናገር ፤ በአንደበቱም ሰውን የማይሸነግል ፤ በባልንጀራውም ክፋትን የማያደርግ እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር ምሎ ባልንጀራውን የማይከድ እንዲህ የሚያደርግ ለዘላለም አይታወክም ብሎአል መዝሙር ፲፬ ከቁ· ፩—፭

እርግጥም ዲዮጋንም ሆነ ዳዊት እንደተናገሩት ቀን በመብራት የሚፈለገው እንዲህ ያለው ሰው ነው ። ለምሳሌ እንደ አዝማሪ የመሰንቆውን ወይም የክራሩን ቅኝት እየለዋወጠ ልዩ ልዩ ዓይነት ዜማ በመዘመር አድማጮችን በአንድነት እንደሚያስደስት ሁሉ መልካም አሠሪም ሥራንና ሠራተኛውን በአንድነት እንዲተባበሩካደረገ ምርት ይበዛል አገር ወደ ዕድገት ደረጃ ይደርሳል በዚህ መንገድ ኅብረተሰቡ ይበለጽጋል እኩልነት ፤ ተባብሮ መሥራት ፤ ሰላምና ፍትሕ በተግባር ይተረጐማሉ ማለት ነው ።

ሰንባንቱ ፋዘር ቴምፐል እንደጻፈው «ኑሮ የጋራ ነው መኖርም ደስታውንም ችግሩንም አብሮ ለመካፈል ነው በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የግል የሆነ ነገር የለም አንዱን የሚመለከተው ሌላውንም ይመለከታል የጥቂቶች ኃይል የሁሉም ኃይል ነው የጥቂቶችም ድካም የሁሉም ድካም ነው ከሠራተኞችና ከታታሪዎች ጋር በኖርን ቁጥር ሠራተኞችና ታታሪዎች



www.ethiopianorthodox.org

እንሆናለን የነርሱ ኃይል እኛንም ያንሳናል ከሰነፎችና ከደካሞች ጋር ብንኖርም የነርሱ ስንፍና ይጋባብንና እኛን ወደታች ይጐትተናል» ብሏል ።

እርግጥም በኅብረት መሥራትና ከሠራተኞች ጋር እየሠሩ መኖር የሕይወት ዋስትና ሲሆን ከሰነፎች ጋር መኖር ደግሞ ሥራን ወደ ኋላ ስለሚጐትት ሕይወት የተለየው በድን ነው።

ይህንንም እውነት ሊያደርገው የሚችለው በየጊዜው የሚነሱት የሥራ ሰዎችና የመንፈስም ሆነ የጥበብ ምሁራን ሌት ከቀን ያለ ዕረፍት በሥራ የሚናወዙትና ሕይወታቸውንም በሙሉ ለኅብረተሰቡ በድካምና በልፋት የሚያሳልፉት ሥራ የተባለው ቃል በምርት እንዲተረጐም ታሪክም የክብር ቦታውን ይዞ እንዲገኝ በማለት ነው ። ይህም በቃል ብቻ ተውጦበተግባር ሳይገለጽ ከቀረ ግን ሥራ ያለትርጉም ስለሚቀር የታሪክም ሆነ የሥራ ብርሃን ለሚሠራላት ትውልድ ጨለማ እንጂ ብሩህ ሊሆን አይችልም ስለዚህ በዕውቀት እየተደራጀ ፤ እራሱን የሚችልና ሌላውንም የሚያስችል አገሩንም እንድትበለጽግ ሌት ከቀን የሚጥር ፤ ስለ ሀገሩና ስለ ሕዝቡ ኑሮ የሚታገል ፤ ለወገኑ ሀብትን ለማበርከትና ትውልድንም የዕውቀት ከበርቴ ለማድረግ የሚጣጣር አገራችንም ቤተ ክርስቲያንም እንደ ዲዮጋን በመብራት ሰው የሚፈልጉበት ጊዜው አሁን ነው ።

ወጥ የሚጣፍጠው በድስቱ ትልቅነት ሳይሆን ከአሠራሩ ነው ሥራም ጣፋጭ የሚሆነው በትምህርት ብዛት ሳይሆን ዕውቀት በሥራ የተገለጸ እንደሆነ ነው በዚህ አኳኋን የሕክምና ባለሙያ የሆነ ሁሉ ያገኘውን እውቀት በሥራ እየገለጸ ሕዝቡን በማከም በሽታ ጠፍቶና ሁሉም ጤነኛ ሆኖ ወደ ሥራ ከተሰማራ ጤነኛ ዜጋ ነወና ይፈለጋል ።

አስተማሪም ድንቁርና እንዲጠፋ ዕውቀት እንዲስፋፋ ካደረገ ጥሩ ሰው ነውና ይፈለጋል ዳኛም ቀጠሮ ሳያበዛ በእውነት ስለ እውነት ከፈረደ መልካም አገልጋይ በመሆኑ ይፈለጋል ነጋዴም ተመኑን ጠብቆ የተፈቀደለትን ትርፍ እያገኘ ደንበኞቹን በሚገባ ካስደሰተ ታማኝ ሰው ነው ይፈለጋል ።

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ተባብረው ሲሠሩ ነው ኅብረተሰብ ሊበለጽግ የሚችለው ሰዎች የተፈጠሩት እርስ በርስ እንዲረዳዱ ፤ የኑሮ ቀንበርን አብረው እንዲሸከሙ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

www.ethiopianorthodox.org